የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

ቀን/Date: ሕዳር 10 2013

ቁጥር / Ref: ሳካት /መ/ተ/ል 9.1/7288/13

**ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች**

**ባሉበት**

ጉዳዩ፡- ውጪ ሀገር የትምህርት እድልን ይመለከታል፡፡

መንግስት የከፍተኛ ትምህርት መምህራንን የሙያ ደረጃ በማሻሻል የመምህራንን ሙያና ደረጃ ስብጥር ለማሳደግ የተቀመጠውን ግብ እውን ለማድረግ በሀገር ውስጥ ያለውን አቅም አሟጦ መጠቀምና በውጭ ሀገራትም በተመረጡ የሙያ ዘርፎች መምህራንን በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡ ቀደም ሲል በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማኔጅመንት ውሳኔ ለሁሉም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተጻፈው ደብዳቤ መሰረት ወደ ህንድ ሀገር በመንግስት ስፖንሰርነት የሚላኩ መምህራን ከእንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ ትምህርት ዘርፍ በግላቸውም ሆነ በኤምባሲ የትምርት ዕድል ሲያገኙ በተቋሙ በኩል ሲቀርብ እንዲማሩ መወሰኑ ይታወቃል፡፡

ስለሆነም በሀገር ውስጥ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ እና በህግ የሙያ መስኮች በ3ኛ ዲግሪ የማስተማር አቅም ዝቅተኛ መሆኑን ከተቋማትና ከመምህራን በቀረበው ጥያቄ መሰረት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ማኔጅመንት በኤምባሲ በኩል የትምህርት ዕድል ስለማግኘታቸው በደብዳቤ ለተፈቀደላቸው እና በአሁኑ ጊዜ በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት በኦን ላይን የመጀመሪያውን ሰሚስተር ትምህርት የጀመሩ መምህራን ለ2013 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ብቻ የተፈቀደ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ዶ/ር ኤባ ሚጀና ነገሮ
የከፍተኛ ትምህርት
አካዳሚክ ጉዳዮች
ዳይሬክተር ጄኔራል

ግልባጭ፤

- ለትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
- ለከፍተኛ ትም/ አካዳሚክ ጉ/ዳይሬክቶሬት ጀነራል
- ለመምህራንና ተማሪዎች ልማት ዳይሬክቶሬት

ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር

www.moshe.gov.et info@ethernet.edu.et www.facebook.com/SHE.Ethio

☏ +251 – 1- 8332789 ፋክስ/FAX: ✉ :- 23976 ኮድ/CODE 1000